ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

እሮብ ግንቦት 20 2000 ዓ.ም

---

**የኢትዮጵያ የጠበቆች መሃበር ተለጣፊ ሊበጅልት ነው፡፡**

ተለጣፊዎች በማቆም የታወቀው የመለስ፣ የበረከትና የስብሃት የማፍያ ቡድን አዲስ ተለጣፊ ለማቆም ሽር ጉድ እያለ ነው፡ ያሁኖቹ ባለተረኞች ደግሞ የሃገሪቱ የህግ ባለሙያተኞች ጠበቆች ናቸው፡፡ ጠበቆች በፍላጎታቸውና በነጻነት ያቆሙትን ማህበር ህልውና አጥፍቶ በወያኔ ኢህአዴግ አምሳል በተፈጠረ በሌላ ተለጣፊ ድርጅት ለመተካት ሴራው ተጀምሯል፡፡ አገዛዙ የጠበቆችን ማህበር አላውቅም፣ የማህበሩ ፈቃዱ እንዲታደስ አልፈቅድም እያለ ነው፡፡ በቅረቡ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት በመለስ ዜናዊና በ አድርባይነት መመዘኛ በተመረጡ ጠበቆች መሀል ወይይት ተደርጎ ነበር፡፡ ይህ ወይይት የወቅቱን የጠበቆች መሃበር ፕሬዚዳንት አቶ ታምሩን ያገለለ፤ ለአገዛዙ ያደገደጉ እንደ ሚሊዮን አሰፋ፣ የመለስ ዜናዊና የህወሃት የግል ጠበቃ የሆነውን መብረሃቱ ዮሃንስንና ሌላ ለወያኔ-ኢህአዴግ ነፍሱን ለመሸጥ የተዘጋጀ አጎብዳጅ ማርቆስ የሚባል ጠበቃ የተሳተፉበት መሆኑ ታውቃል፡፡ መለስ ዜናዊ ጠበቆች ለተቃዋሚው ጥብቅና በመቆም እራሳቸው ተቃዋሚ መሆናቸውን አሳይተዋል በሚል ቂም ተገፋፍቶ ድርጅታቸውን ከላይ በተጠቀሱ ግለሰቦች በሚመራ ተላፊ የጠበቆች መሃበር ሊተካ መቁረጡን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡ የመለስ የማፍያ ቡድን ስልጣን ከመያዙ በፊት ብአዴን አሆዴድ የሚባሉ የኢህአዴግ ተለጣፊ ድርጅቶች መፍጠሩን፣ ነጻ የጋዜጠኖች፣ የመምህራንና የሰራተኞች ማህበራትን በማፍረስ በምትካቸው ተለጣፊ መሃበራት መፍጠሩን፣ ከእዛም አልፎ እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በማጥፋት የራሱን ተለጣፊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በማቆም እስካሁን ያለምንም ሃፍረት የፈጸመውን ድርጊት በጠበቆች ላይ ቢደግመው የማያስገርማቸው እንደሆነ የሚፈጸመው በደል ያንገበገባችው የህግ ባለሙያተኖች ለግንቦት ዜና አስረድተዋል፡፡